የረቡዕ የካቲት 22 1998 ዓ ም ( የማርች 1  2006)

## የፍኖተ ዴሞክራሲ ሐተታ

<u>በአዲስ ራዕይ፥ አዲስ  ኅብረት፥ ለአዲስ  የትግል ስልት</u>

ኢትዮጵያ ሀገራችን እንደ ጃፓንና እንደ ሌሎቹ ተመሳሳይ ሀገሮች አንድ ቋንቋና ዕምነት አንድ ዘርና ባኅል፥ አንድ መልክና ገፅታ፥ እንዲሁም ታሪክ ያላቸው ዜጎች የሚኖሩባት ሀገር ሆና ብትሆን ኖሮ፥ አሁን ያለችበት ብሔራዊ ችግር ይህን ያህል የጎላ ባልሆነባት ነበር የሚሉ ታዛቢዎች ቁጥር ቀላል ባይሆንም፥ የሶማሊያን ችግር የሚያውቁ በዚህ አይስማሙም:: በሌላ ገፅታዋ ደግሞ፥ ሀገራችን የብዙ ብሔር ብሔረሰብ ሀገር መሆኗ ፥ ዛሬ በዘር ላይ የተመሠረተ አምባገነን ሥርዓት በመስፈኑ ምክንያት የአሉታዊ አንደምታ ሰለባ ለመሆን በቃች እንጅ፥ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ቢመሰረት ኖሮ ልዩነቱ እንደፀጋ እንደ ጥንካሬና እንደ ታላቅነት ይቆጠር ነበር የሚሉና የወደፊት ዕድሏንም ባውንታዊ ተስፋ ላይ የሚያዩላት ተመልካቾች አሉ:: ሀገራችን በጉራማይሌ ገፅታ የተጎናፀፈ  መልክ መኖሯ፥  በዕርግጥም ውበቷን ያደምቅላት እንደሁ እንጅ፥ የችግሮቿ ሁሉ ምክንያትና ማጠየቂያ ሊሆን አይችልም:: ምክንያቱም እንደ ሀገራችን ሁሉ ተመሳሳይ ገፅታና ይዘት ያላቸው  ሌሎች በርካታ የዓለም ሀገሮች፥ በተለያየ ገፅታቸው ላይ የተመሠረተና ሁሉንም በሚያቅፍ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ስለሚተዳደሩ ይመስለናል:: ኢትዮጵያ ሀገራችን ለዜጎቿ ይህንን ፀጋ ለማጎናፀፍ ለምን እንዳልበቃች፥ እንዳልቻለችና ለምንስ እንዳልታደለች መጠየቅ የሚገባው ሁሉም ዜጋዋ ነው ብለን እናምናለን:: ይህን መሠረታዊና ቋሚ ጥያቄ ጠይቆ መፍትሄውን መፈለግ ደግሞ፥ የያንዳንዱ ዜጋ ግዴታና ኃላፊነት ነው ብለን ለማመን እንወዳለን::

ከዚህ መሠረታዊ ዕውነታ ጋር ተያይዞ አብሮ ሊታይ የሚገባው ሌላው ዓብይ ጉዳይ፥ በሀገራችን ባኅል፥ ታሪክና እሴት ላይ ያልተመሠረተ የፖለቲካ ሥርዓትም  ሆነ የኢኮኖሚ ንድፍ፥ ችግራችንን ያባብሰው እንደሆነ እንጅ፥ መፍትሔ ሊያመጣልን አለመቻሉ ነው:: እስካሁንም እየተሞከረ ፋይዳ ሊያስገኝልን ያልቻለውም በዚሁ ምክንያት ይመስለናል ::

“ ለምሳሌ ሕንዶች በጣም ሥልጡን ናቸው፥ ግን:-
አልተቀላቀለም  ከሌላ  ባኅላቸው” እያሉ ቢያቆዝሙት፥ በተግባር ካልተተረጎመ ሰቆቃ ብቻ ሆኖ ይቀራል::  ከዚህ ሰቆቃ ለመላቀቅ ታዲያ፥ <u>በአዲስ ራዕይ ላይ የተመሠረተ አዲስ የጋራ ግንባር ፈጥሮ በአዲስ የትግል ስልት እየታገሉ ሀገርን ማዳን ብቻ ነው::</u> በኅብረት ተጠናክሮ በጋራ ከመታገል

የተለየ መፍትሔ አለመኖሩን ያልተረዱ ወገኖች ካሉ ጊዜው ሳያልፍ እንዲያስቡበት ያስፈልጋል።

እርግጥ በኅብረት ተጠናክሮ በመቆም ይህችን ውድ ሀገር ከገባችበት መከራ ማላቀቅ አስፈላጊ መሆኑ ሁሉም አምነንበታለሁ ካለ፥ ዓመታት ተቆጥሯል። ችግሩ የማመን ሳይሆን፥ በተግባር አለመተርጎሙ ነው። እስካሁን ወያኔን ለማንበርከክ ያልተቻለው በዓለም ተወዳዳሪ ኃይል የማይገኝለት አንድ ድርጅትም ሆነ፥ ወይም ስብስብ፥ ያለዚያም የተወሰኑ ክፍሎች ብቻቸውን የኢትዮጵያን ችግር ማስወገድ ቀርቶ ሊቀርፉት ባለመቻላቸው ነው። በርካታ ድርጅቶች፥ ይህን ዕውነት ለማወቅ፥ ገና መረዳት አልሆነላቸውም ቢባል ማጋነን አይሆንም።

ተወደደም ተጠላ የኅብረ ብሔር እና በብሔር የተደራጁ ክፍሎች፥ ሌላው ቢቀር፥ ኢትዮጵያን እንደ ሀገር ለማቆየት ከፈለጉ፥ ከወሰኑ፥ ከተስማሙ፥ ያላቸው ምርጫ አንድ ብቻ ይሆናል። ይኸውም፥ እስከአሁን ድረስ ተደጋግሞ ተደጋግሞ የሚነገረውና ግን፥ እስከሁን ምላሽ ያላገኘው፥ሁሉንም ያካተተ ጠንካራ የኅብረት ግንባር የመፍጠሩ ጥያቄ ነው። በተለያዩ አጋጣሚዎች ልዩ ልዩ ሙከራዎች ቢደረጉም እስካሁን ይህ ዕውን አልሆነም። ሌሎቹን ሙከራዎች ለታሪክ ግንዛቤ እንተዋቸውና ከአለፉት አስራ ስድስት ዓመታት አንስቶ ለኅብረት ግንባር የተደረጉትን ሙከራዎች እንኳን ብናወሳ፥ ከኢዴኃቅ ምሥረታ ጀምሮ ፓሪስ አንድና ፓሪስ ሁለት፣ግዮን ወዘተ የተሰኙትን ሙከራዎች ጨምሮ፥ ያማራጭ ኃይሎችን ስብስብ አክሎ፥ አሁን ከተደረሰበት ሂደት ኅብረትና ቅንጅት የሚባሉትን ጥረቶች አጠቃልሎ መናገር ይቻላል። ሁሉም የሰጡት ጥቅም ባይካድም ወሳኙን ድል ያልተቀዳጁት፥ የሀገሪቱን መሠረታዊ ችግር፥ እስከ ዓይነተኛ መፍተሄው ሊያገኙት ባለመቻላቸው ነው ብሎ የኢትዮጵያ ሕዝብ ደምድሟል። የተደረጉት ሙከራዎች ሁሉና ለእነርሱም የተከፈለው መስዋዕት በቀላሉ የሚገመት ባይሆንም፥ የተደረጉት ሙከራዎች ሁሉ ግን የዓላማቸውን የመጨረሻ ግብ ሊመቱ አልተቻላቸውም። ማለትም፥ ወያኔን ከሥልጣን አስወግደው ኢትዮጵያን ከጥፋት ለማዳን አልተሳካላቸውም። በአጭሩ ፈተናቸውን አላለፉም። ሁሉም ባይሆኑ የተወሰኑት የኢትዮጵያን ሕዝብ አመኔታና ክብር አላተረፉም ብንል ደግሞ ስህተት አይሆንም።

ይህንን ጉዳይ ዛሬ ለማንሳት የተገደድነው፥ የሁኔታው አስገዳጅነት እየገፋና የትግሉም ሂደት መላ ቅጡ እየጠፈበት በመሄዱ ነው። መላ-ቅጡ የጠፋበት ትግል ደግሞ፥ ሀገርን ነፃ ለማውጣት የሚያስችል ራዕይም ይሁን ስልትና ዕቅድ ለማውጣት አይችልም። በአብዛኛው የዳበሳ ጉዞ መሆኑ፥ የትግሉን ፈርና አቅጣጫ እንዲሰምር አላደረገውም።

ይህን ዕውነት ለመዳሰስ የምንቃጣው ዛሬ፥ እስካሁን ድረስ የተጓዘው የትግል ሂደት፥ ዓላማችንን ለመምታት ስላላስቻለን፥ በግድ በአዲስ ራዕይ ላይ የተመሠረተ አዲስ ጠንካራ የተቃዋሚ ድርጅቶች ኅብረት መሥርቶ፥

ትግሉን በአዲስ ስልትና ዕቅድ ማካሄድ አስፈላጊ መሆኑን ለመጠቆም ነው። ይህ ክሰተት በግድ መፈጠር አለበት። ይህን ክስተት ዕውን ሊያደርጉ የሚችሉ ደግሞ የሚከተሉትን መሠረታዊ ዕውነታዎች የተቀበሉ ድርጅቶች ሲሰባሰቡ ብቻ ይሆናል።

ሀ) ሁሉም በኢትዮጵያ ሕዝብ እኩልነትና አንድነት ማመን ይጠበቅባቸዋል።

ለ) በሀገሪቱ የግዛት ልዕልና÷ ብሔራዊ ነፃነትና በዜጎቿም ሉዓላዊነት ማመንን መቀበል አለባቸው።

ሐ) በዴሞክራሲያዊ ሥርዓተ-መንግሥት÷ በሕግ የበላይነትና በኢትዮጵያ ሕዝብ የነፃነት ልዕልና ማመን መቀበል አለባቸው።

መ) የወያኔን የዘር ፖለቲካ የሚቃወሙና ይህንንም ሥርዓት ለውጦ በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመተካት የተስማሙ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል።

ሠ) ከሁሉም በላይ ደግሞ÷ ከ ሀ እስከ መ ፊደል ተራ የተዘረዘሩትን መሠረታዊ አቋሞች እስከ መጨረሻው እንደ ዓላማቸው አንግበው ለመታገል የተስማሙ ድርጅቶች÷ በፊርማቸው ያፀደቁቱን ስምምነት አክብረው እስከ መጨረሻው የትግሉ ግብ ድረስ መቀጠል መቻል አለባቸው። ይህን ካደረጉ÷ ሀገራቸውን ከወያኔ ጥፋት ከማዳናቸውም በላይ÷ ከኀልፈተ-ወያኔ በኋላ ለምትገነባው ኢትዮጵያ ወሳኝ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ። ይህ ሁሉ ሀገራዊ ምኞትና ራዕይ ዕውን ሊሆን የሚችለው ግን÷ አዲስ ራዕይን መሠረትና አቅጣጫ ያደረገ÷ አዲስ የተቃዋሚ ጎራ ፈጥሮ አዲስ የትግል ስልትና ግብ ነድፎ አዲስ የትግል ምዕራፍ ሲከፈት ሲቻል ነው።

ለአዲሲቱ ኢትዮጵያ÷ ለነገዋ ኢትዮጵያ÷ ለሃያ አንደኛው ምዕተ ዓመት ኢትዮጵያ የሚሆን ራዕይና ብሔራዊ አጀንዳ አንግቦ የማይታገል የኅብረት ግንባር÷ አንድ ምዕራፍ የማይራመድ መሆኑ ያለፉት 15 ዓመታት ተመክሮ በሚገባ አስተምሯል። ሆኖም ግን÷ ያለፉትን የችንፈትና የጥቃት ዘመናት÷ የውርደትና የሀፍረት ዓመታት÷ የሀዘንና የሰቆቃ ጊዚያት ወደ ጎን ትቶ÷ ብሔራዊ ትኩረቱና ሕዝባዊ ርብርቦሽ መሆን የሚገባው÷ የመለስ ዜናዊን ቡድን አስወግዶ ኢትዮጵያንና ሕዝቧን በማዳኑ ላይ እንጅ÷ እርስ በእርስ በጭራሮ በመጨፋጨፉ ላይ አይደለም። ለዚህ ደግሞ ከአድማስ ባሸገር ማየትን÷ ከየግል ድርጅት ጥቅም በላይ ማሰብንና ከግለሰብ ከንቱ ውዳሴና አላፊ-ጠፊ ዝና ውጭ መመልከትን ይጠይቃል።

በሌላ በኩል ደግሞ÷ ጠቅላላው ኅብረትስብ÷ በተለይም ደግሞ ምሁሩና የነቃሁ የበቃሁ ነኝ የሚለው ክፍል÷ በድርጅቶች መካከል ያለውን÷ የሚንፀባረቀውንና የሚታየውን ጥፋትና ስኅተት ለይቶ በማወቅ÷ ጥፋተኛውን÷

ከአሳጠፋው እየፈረጀ ፍርድ መስጥት አለበት። በጅምላ ፍርድ እየበየኑ፥ እንዲያው በጠቅላላው ሁሉንም ድርጅቶች ጥፋተኞች ናቸው ቢሉት፥ ትክክል ፍርድ አይሆንም። "ፍርድ ለግጫ" ነው እስከተባለ ድረስና በዕርግጥ ሁሉም ለሀገር ማዳኑ ጉዳይ ከልብ ካሰበበት፥ አጥፊውን አጥፊ፥ አልሚውን አልሚ ማለት ይኖርበታል። የሀገር ጉዳይ በይልኙታና በምንቸገረኝነት ሊተው የሚገባ አይሆንም።

የሀገራችን ሁኔታ አሁን ከደረሰበት አኳኋን ሲታይ፥ ብዙ እጅግ ብዙ ተግባር እንደሚጠብቀን፥ሁላችንም ልንገነዘበው ይገባናል። አንዱ መሥዋዕት ከፋይ ሌላው ተመልካች ልንሆን አይጠበቅብንም። እያንዳንዱ ዜጋ የሚጠበቅበትን ካሟላ፥ የሀገራችን ችግር በፍጥነት እንደሚወገድ መጠራጠር አይችልም። ድርጅቶቹ ብቻ ይታገሉ፥ እነርሱ በጀመሩት ይጨርሱት የሚለው አመለካከትና አስተሰሳብ፥ ምናልባት ለጊዚያዊ የኃላፊነት መሸሸጊያ ይረዳ እንደሁ እንጅ፥ በታሪክም ይሁን በትውልድ ፊት ከመጠየቅ አያድንም። እንደ ሸማኔ መወርመሪያ፥ ድርጅቶች በኅብረተሰቡ፥ ኅብረተሰቡም በድርጅቶች እንዲሁም ድርጅቶች እርስ በእርሳቸው ቢነታረኩ፥ ያው ዞሮ ዞሮ የምተጎዳው ሀገሪቷ ብቻ ነች። ይህም በመሆኑ፥ እስካሁን መለስና ግብራበሮቹ የተጎዱት ነገር የለም። መለስ ዜናዊ አንድ ሐሙስ ቀርቶታል የሚለውን አባባልና አስተሳሰብ ሰርዞ፥ በአዲስ የትግል ስልትና ዕቅድ እየተዋደቁ ሀገርን ማዳን ከታሪክና ከተተኪው ትወልድ ወቀሳ ያድናል። ለኢትዮጵያ ጥፋት በመጀመሪያ ተጠያቂው አሁን በዘር ላይ የተመሠረተው ሥርዓትና አቀንቃኞቹ ብቻ ቢሆኑም፥ ኢትዮጵያን ሲያጠፉ ዝም ብሎ የተመለከታቸው ሁሉ ከኃላፊነት ሊያመልጥ የሚችል አይመስለንም።

አዳም በሄዋን፥ ሄዋን በእባቧ፥ እባቧ በዳቢሎስ፥ ዳቢሎስ ፥በእንጦሮጦስ፥ አንዱ በሌላው፥ ሌላው በፈረደበት፥ የፈረደበት በተያዘው፥ የተያዘው በተረዘዘው፥ ላይ ጣት እየቀሰረ፥ የራሱን ስህተት እየሰወረ፥ የሌላውን መልካም ተግባር እየቀበረ፥ ትግል ግቡን ይመታል ብሎ የሚያስብ ካለ፥ መካሪ ያጣ መሆን አለበት። ይህ እርስ በእርስ ጣት የመጠቋቆሙ ሁኔታ እየቆመ በጋራ ጠላት ላይ የመረባረቡ ተግባር መቀጠል የተቃዋሚ ድርጅቶች ዓይነተኛ ትኩረትና ዒላማ ሊሆን ይገባዋል።

ይህንን መሠረታዊ መርህ፥ ውጤት ሊያስመዘግብ በሚያስችል ተግባር ለመለወጥ፥ በአዲስ ራዕይ፥ አዲስ ኅብረት፥ አዲስ የትግል ስልት፤ዕቅድና ግብ መሠረት መታገል አማራጭ አይኖረውም!!!